# ማሕበር ተጋሩ ሰሜን ኣሜሪካ (ማ.ተ.ሰ.ኣ)

# UNION OF TIGREANS IN NORTH AMERICA (UTNA)

P.O.BOX 73736
Washington, DC 20056
utnaoffice@gmail.com

Tel. (202) 862-4367
Fax. (202) 265-8703
www.utna.org


**ቀን፡- ጁን 01፣ 2018**

ግልጽ ደብዳቤ

ከ፡- የትግራይ ተወላጆች ማሕበር በሰሜን አሜሪካ ማእከላዊ ጽ/ቤት
ዋሽንግተን ዲሲ

ለ፡- ክቡር ዶ/ር አብይ አሕመድ
የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ ሚንስትር እና የኢህአዴግ ሊቀ መንበር
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- በውጭ ሀገራት በሚንቀሳቀሱ የሚዲያ አውታር ላይ ስለተላለፈ ውሳኔ ይምለከታል

በመጀመርያ የማክበር ሰላምታችንን በማስቀደም ለራስዎና ለመላ ቤተሰብዎ ሰላምና ጤንነት ለስራዎ መቃናት ያለን መልካም ምኞት በማህበራችን አባላትና ደጋፊዎቻችን ስም ለመግለፅ እንወዳለን:: በመቀጠል እንደሚታወቀው፣ ከተመሰረተ 44 ዓመታትን ዕድሜ ያስቆጠረው ማሕበራችን በትግሉ ዘመን ሀገራችን ኢትዮጵያ ከአስከፊው ጨቋኙ እና ጸረ ህዝብ የደርግ ስርዓት ለማላቀቅ በተደረገ መራራ ትግል እስከ የህይወት መስዋዕትነት የከፈለ ማሕበር ነው። እንዲሁም በሽግግሩ ወቅት ሁሉም ኢትዮጵያዊያን የተሳተፉበት ሕገ መንግስታዊ ስርዓት የመትከል ፈታኝ ስራ እንደ አንድ ፈር ቀዳጅ ህዝባዊ አደረጃጀት፣ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን በሀገራቸው ጉዳይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያግባባ እና ያቀራረበ ማሕበር መኾኑ ይታወቃል።

ከነዚህ ወሳኝ ሀገራዊ ሁነቶች ላይ ካበረከተው አስተዋጽኦ በተጨማሪ፣ ላለፉት 27 ዓመታት በሀገራችን በሰላም፣ በልማትና በዲሞክራሲ መስክ ለተገኙ ድሎች የበኩሉን ሚና የተጫወተ ማሕበር ነው። አሁን ባለንበት ወቅትም ከምን ጊዜውም በላይ በሀገራችን ዲሞክራሲያዊ አንድነት እና የብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች እኩልነት ያረጋገጠው፣ (ሕገ መንግስታችን በማጽደቅ ያደረገውን አስተዋጽኦ ግምት ውስጥ ባስገባ)፣ ለሕገ መንግስቱ መከበር እና ተፈጻሚነት ጠንክሮ በመስራት ላይ ይገኛል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ባለፉት ሶስት አመታት በሀገራችን የታየው የሰላም መድፍረስ እና የሀገር አለመረጋጋት በሕገ መንግስታዊ አሰራር ብቻ መፍትሔ እንዲያገኝ በተደጋጋሚ በሚያወጣቸው የአቋም መግለጫዎች ላይ አስረድቷል።

እንደ አንድ ህዝባዊ ማሕበር፣ ሀገራችን ከነበረችበት አስቸጋሪ ሁኔታ ለማውጣት የሀገራችን ህዝቦች ሰከን ባለ ሁኔታ በሰላማውዊ መንገድ ብቻ ጥይቄዎቻቸውን እንዲያቀርቡ፤ የሰው ህይወት እንዳይጠፋ አሳስበናል። መጨረሻ ላይ ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ እና መንግስት ያካሄዱት ስር ነቀል የተሀድሶ ለውጥ እንዲሁም ሰላማዊና ሕገ መንግስታዊ የስልጣን ሽግግር በማድነቅም ድጋፋችንን ገልጸናል።

በሀገራችን የሚደረግ ሕገ መንግስት የማክበር እና የመተግበር ስራ ውስጥ አንዱ የሆነው ዜጎች መረጃ የማግኘት መብት ሳይሸራረፍ እንዲፈጸም መንግስት የሚያደርገውን እንቅስቃሴ የሚበረታታ ቢሆንም የህዝቦች ተከባብሮ የመኖር እሴቶች የሚንድ እና ወደ መባላት እና መጠፋፋት የሚወስዱ አፍራሽ የሚዲያ አውታር ተግባሮችን ግን

አጥብቀን የምንታገል መሆኑን ሊሰመርበት ይገባል። ለዚህ ማሳያ ይሆነን ዘንድ ባለንበት ሀገረ አሜሪካ መቀመጫውን ያደረገ ኢሳት የተባለ የሳተላይት ቴሌቪዥን ድርጅት በትግራይ ህዝብ ላይ በተከታታይ ሲያካሂደው የነበረ የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ ፈሩን ለቆ እንደ አውሮፓዊያኑ አቆጣጠር በ2016 ኦገስት ወር ላይ በግላጭ በትግራይ ህዝብ ላይ የዘር ማጥፋት ጥሪ አዋጅ አስተላልፏል። ማሕበራችን የህዝባችን ድህንነት ከምንም በላይ ቅድሚያ ሰጥቶ የሚሰራ ህዝባዊ አደረጃጀት እንደመሆኑ መጠን፣ አስፈላጊውን መረጃ በማሰባሰብ እና በማደራጀት ይህ ጉዳይ በአካባቢው ሕግ መሰረት የማሕበራችን እና የሕግ ባለሞያዎች ጥረት ታክሎበት እየታየ ነው። በኢትዮጵያ ሕገ መንግስት ዓንቀጽ 28 ንዑስ ዓንቀጽ አንድ (1) መሰረት የዘር ማጥፋት ወንጀል ከባድ ወንጀል እንደሆነ ይደነግጋል። ኢሳት ይህንን ሕግ በመተላለፍ በትግራይ ህዝብ ላይ የዘር ማጽዳት ተግባር እንዲፈጸም በግላጭ ጥሪ አቅርቧል። ይህንን ተከትሎም የትግራይ ተወላጆች በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች በተለይ በሰሜን ጎንደር ጥቃት ደርሶባቸዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በሀገራችን እየተካሄደ ያለው የተሃድሶ ለውጥ በተለይ ሰላም እና የሕግ የበላይነት ለማስፈን እንዲሁም የይቅርታ የሀገራዊ መግባባት ጥረት ድጋፋችንን ብንገልጽም፣ ኢሳት የተባለ ጸረ ህዝብ የዘር ጭፍጨፋ ሰባኪ የሳተላይት ቴሌቪዥን ጣቢያ በተለይ ለድርጊቱ በግልጽ ይቅርታ ባልጠየቀበት እና በተከታታይ በትግራይ ህዝብ ላይ የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ እየነዛ በለበት ሁኔታ፣ ወደ ሀገር ገብቶ ስራውን እንዲያካሂድ ከመንግስት በኩል ጥሪ መቅረቡ ግን በእጅጉ አሳዝኖናል። ህዝቦች ላይ ያነጣጠረ ጥላቻ ሄዶ ሄዶ ሀገር ማፍረሱ አይቀሬ ነው። ስለሆነም ይህ ድርጊት በማንኛውም ህዝብ ላይ እንዲፈጸም ፈጽሞ ሊፈቀድ አይገባም። ስለዚህ ማሕበራችን እያካሄደ ያለዉን የሕግ ክትትል አጠናክሮ እንደሚቀጥልበት እየገለጸ፣ መንግስት ውሳኔውን ሀገር የሚጎዳ እና የትግራይን ህዝብን ከሌላው የነጠለ እና በጣም ከልብ ያሳዘነ መሆኑን በመረዳት የተሰጠው ውሳኔ እነዚህን የኢሳት ሳተላይት ቴሌቪዥን ድርጅት ድርጊቶች ግምት ውስጥ ያላስገባ በመሆኑ፣ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስተር በድጋሜ እንዲያዩት ማሕበራችን ጥሪውን በትሕትና ያቀርባል። ከዚህ በመለስ ባለው ግን ማሕበራችን መንግስት ሀገራዊ መግባባትና እርቅ ለመፍጠር የሚያደርገውን ጥረት ከልብ አምኖና ደግፎ እንደሚሰራ በዚህ አጋጣሚ ይገልጻል።

ከአክብሮት ጋር!

የትግራይ ተወላጆች ማሕበር በሰሜን አሜሪካ ማእከላዊ ጽ/ቤት
ዋሽንግተን ዲሲ

ግልባጭ:-

ለኢትዮጵያ ኤምባሲ በዩናይትድ ስቴትስ ዋሽንግተን ዲሲ
ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት
ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን